መልእክት ሁለት

## በባቢሎን ካለው ምርኮኝነት ከመመለስ በኋላ
## በመልካሚቱ ምድር የመኖር ወሳኝ ገጽታዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ዜና 4፡10፤ 9፡1፤ 16፡8-12፣ 16-18፤ 29፡10-20፤
2 ዜና 20፡15-22፤ 36፡22-23

**I. የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ የአዲስ ኪዳን አማኞችን በምሳሌ የሚያሳይ፣ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ የሚያሳይ ምሳሌ ነው—2 ዜና 36፡22-23፤ 1 ቆሮ. 10፡6፣ 11።**

**II. ይሁዳ ወደ ባቢሎን የተማረኩት ከአለመታመናቸው የተነሣ ነበር፤ ስለዚህ፣ ከምርኮ የተመለሱት ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆን ነበር—1 ዜና 9፡1፤ 1 ቆሮ. 4፡1-2፤ 7፡25፤ 2 ጢሞ. 2፡13፤ ራእ. 17፡14፡-**

ሀ. እግዚአብሔር ኢኮኖሚውን ለመፈጸም እና እኛን ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ ለመምራት ታማኝ ነው—ሰቆ. 3፡23።

ለ. እንደ ታማኙ አምላክ፣ እግዚአብሔር ራሱን ሊክድ አይችልም፤ የራሱን ማንነት ሊክድ፣ ከዚያ በተጻራሪ ሊሄድ አይችልም—2 ጢሞ. 2፡13።

ሐ. እርሱ ከታማኝነት ባሕርይው ጋር ወደ ውስጣችን ሲሠራ፣ እኛን ይሆናል፣ እኛም በታማኝነት ባሕርይው እርሱን እንሆናለን—1 ቆሮ. 7፡25፤ 2 ጢሞ. 2፡13።

1. እግዚአብሔር የራሱን ማንነት መካድ እንደማይችል እንዲሁ፣ እኛ በእርሱ ከተቀናበርን በኋላ የራሳችንን ማንነት መካድ አንችልም—ተዛ. ኤፌ. 3፡16-17።
2. እንደ እግዚአብሔር ምሥጢራት መጋቢዎች ታማኝ መሆን የምንችለው እና የምንሆነው በዚህ መንገድ ነው—1 ቆሮ. 4፡1-2።
3. በታማኙ እግዚአብሔር ስለተቀናበርን፣ ለእርሱ ታማኝ መሆን አለብን፤ ማንነታችን፣ ቅንብራችን ከዚህ ሌላ እንድንሆን አይፈቅድልንም።

መ. ታማኝ፣ የታመንን መሆናችን ጌታ ለእኛ የወሰነልንን መጋቢነት መፈጸም ማለት ነው—ቁ. 1-2፤ 7፡25፤ 1 ጢሞ. 1፡12።

ሠ. ጌታ ለውጊያ በአርማጌዶን ሲመጣ፣ የጌቶች ጌታ እና የነገሥታት ንጉሥ ይሆናል፣ ከእርሱ ጋር ያሉት ድል ነሺዎች "የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም" ይሆናሉ—ራእ. 17፡14፤ 19፡11-21።

**III. ከባቢሎን ምርኮ ወደ መልካሚቱ ምድር የተመለሱት በሙሉ ያሕዌን እንዲያውቁት፣ እንዲታዘዙት እና እንዲያመልኩት ታዘው ነበር—1 ዜና 16፡8-14፡-**

ሀ. *እግዚአብሔር* የእግዚአብሔርን ኃይል እና ከፍጥረታት ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታል፤ *ያሕዌ* እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ያመለክታል።

ለ. ያሕዌ አምላክ ኃይለኛ የሆነው ብቻ ሳይሆን ወደ ሰው የሚቀርበውም ጭምር ነው—ዘፍ. 2፡4፣ 8፣ 15-16፣ 18-19፣ 21-22።

ሐ. *ያሕዌ* ማለት "ያለና የሚኖር" ማለት ነው፣ ያሕዌ በራሱ የሚኖር እና ሁሌም የሚኖር ዘላለማዊ፣ በጥንት የነበረ፣ አሁን ያለ እና ለዘላለም ወደፊት የሚኖር መሆኑን ያመለክታል—ዘጸ. 3፡14፤ ራእ. 1፡4።

መ. የሆነው ያሕዌ ብቻ ነው—ዕብ. 11፡6፡-

1. መሆን ያለው ይህ ልዩና ብቸኛ ማንነት ታላቁ "መሆን" ነው፤ የ*መሆን* ግስ ለእኛ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ብቻ ነው መተግበር የሚችለው።
2. እግዚአብሔር አጽናፍ ዓለማዊው መሆን፣ እውነተኛው መሆን ነው፤ እግዚአብሔር ብቻ እኔ ነኝ ነው፤ እርሱ ብቻ መሆን አለው።

ሠ. *ያሕዌ* ለመኖር እና ለፍጻሜ የሆነ የእግዚአብሔር ስም ነው—ዘፍ. 17፡1፤ 28፡3፤ 35፡11፤ ዘጸ. 3፡14፤ 6፡6-8።

ረ. ያሕዌ ለዘላለም ስለሚኖር እና የ*መሆን* ግስ እውነታ ስለሆነ፣ የተናገረውን የትኛውንም ነገር ይፈጽመዋል—ዮሐ. 8፡28-29።

ሰ. ዛሬ በጌታ ምለሳ፣ በፍጻሜ ደረጃ ላይ ነን፤ እግዚአብሔርን እንደ ያሕዌ፣ እንደ ታላቁ እኔ ነኝ እየተለማመድነው ነው—ዘጸ. 3፡14-16፤ ዮሐ. 8፡24፣ 28።

**IV. የእስራኤል ልጆች ወደ መልካሚቱ ምድር መመለሳቸው ክርስቲያኖች ከክፍፍል ወደ ቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ፣ ወደ አንድነት መቆሚያ ስፍራ መመለሳቸውን ያመለክታል—2 ዜና 36፡22-23፤ ተዛ. ዘዳ. 12፡1-32፡-**

ሀ. የቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ መቆሚያ ስፍራ መሠረታዊ በሆነ መልኩ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ተግባራዊ ልምምድ ላይ የሚውለው ልዩና ብቸኛው የክርስቶስ አካል አንድነት ነው—ኤፌ. 4፡4፤ 1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡27።

ለ. በአዲስ ኪዳን ባለው መለኮታዊ መገለጥ መሠረት፣ የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ከሦስት ወሳኝ ንጥረ-ነገሮች የተቀናበረ ነው፦

1. የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ቅንብር የመጀመሪያው ንጥረ-ነገር "የመንፈስ አንድነት" (ኤፌ. 4፡3) ተብሎ የሚጠራው የአጽናፍ ዓለማዊው የክርስቶስ አካል ልዩና ብቸኛ አንድነት—ጌታ በዮሐንስ 17 የጸለየው አንድነት—ነው።
2. የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ቅንብር ሁለተኛው ንጥረ-ነገር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት እና የምትኖርበት ልዩና ብቸኛው የአጥቢያ መቆሚያ ስፍራ ነው—ራእ. 1፡11፤ ሐዋ. 14፡23፤ ቲቶ 1፡5።
3. የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ቅንብር ሦስተኛው ንጥረ-ነገር የመንፈስ አንድነት እውነታ፣ ማለትም፣ የመለኮታዊው ሥላሴ ሕያው እውነታ የሆነው የመንፈስ አንድነት ነው—1 ዮሐ. 5፡6፤ ዮሐ. 16፡13።

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ ከሕይወት ጋር የተገናኘ ነው—መዝ. 133፡1፣ 3፤ 36፡8-9።

## V. ወደ መልካሚቱ ምድር የተመለሱት የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን እንዲያስታውሱ ተነግሯቸው ነበር—1 ዜና 16፡15-18፤ ዘፍ. 15፡7-21፦

ሀ. አብርሃም እግዚአብሔር ስለ ዘሩ ለገባው ተስፋ ቃል አመነው፣ ስለ መልካሚቱ ምድር ለገባው ተስፋ ቃል ግን እግዚአብሔርን ለማመን እምነት አጣ—ቁ. 6-8።

ለ. የአብርሃምን እምነት ለማጠንከር፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን በማድረግ የገባውን ተስፋ ለማጽናት ተገደደ—ቁ. 9፡21፦

1. እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን በጸጋው በእግዚአብሔር ኃይል በኩል የሚፈጸም የተስፋ ቃል ኪዳን ነበር—ዮሐ. 1፡14፣ 17።
2. አዲስ ኪዳን የዚህ ቃል ኪዳን መቀጠል ነው—ገላ. 3፡17፤ 4፡22-26።

ሐ. በተሰቀለው እና ከሞት በተነሣው ክርስቶስ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳኑን አደረገ—ዘፍ. 15፡9፤ ሮሜ 6፡5-6፣ 9፦

1. የታረዱት ሦስቱ የከብት አይነቶች ክርስቶስ በስብዕናው ለእኛ መሰቀሉን ያመለክታሉ፣ ሁለቱ ሕያዋን ወፎች ክርስቶስ በመለኮትነቱ ሕያዉ፣ ከሞት የተነሣው መሆኑን ያመለክታሉ—ዘፍ. 15፡9፤ ዮሐ. 11፡25፤ ራእ. 1፡18።
2. ጊደሩ ለሰላም መሥዋዕት ነበር፣ እንስቷ ፍየል ለኃጢአት መሥዋዕት ነበረች፣ በጉ ለሚቃጠለው መሥዋዕት ነበር—ዘፍ. 15፡9፤ ዘሌ. 3፡1፤ 4፡28፤ 5፡6፤ 1፡10።
3. በምሳሌ፣ ዋኖስ መከራ የሚቀበል ሕይወትን ያመለክታል፣ ርግብ የሚያምን ሕይወትን፣ የእምነት ሕይወትን ያመለክታል፤ እነዚህ በምድር ላይ ሳለ የጌታ ሕይወት ሁለት መለያ ባሕርያት ናቸው—ዘፍ. 15፡9።
4. ሁለት የምስክር ቁጥር ስለሆነ፣ ሁለቱ ሕያዋን ወፎች በውስጣችን እንደሚኖረው እና ለእኛ እንደሚኖረው ማንነት የክርስቶስን ምስክር ይሸከማሉ—ቁ. 9፤ ዮሐ. 14፡19-20፤ ገላ. 2፡20።

## VI. በክርስቶስ እንሚያምኑ አማኞች፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና የግል መንፈሳዊ ድንበራችን እንዲሰፉ ያለንን መሻት የሚገልጡ ጸሎቶች ሊኖሩን ይገባል—1 ዜና 29፡10-20፤ 4፡10፦

ሀ. በአጽናፍ ዓለም ሦስት ፈቃዶች አሉ፦ መለኮታዊው ፈቃድ፣ ሰይጣናዊው ፈቃድ እና የሰው ፈቃድ፤ ለእግዚአብሔር በጎ ደስታ ሰው በጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲገልጥና መልሶ ወደ እርሱ እንዲያስተጋባው እግዚአብሔር የሰው ፈቃድ ከእርሱ ጋር እንዲጋጠም እና ሰው ከእርሱ ጋር አንድ እንዲሆን ይፈልጋል—ማቴ. 6፡10፤ 7፡21፦

1. የጸሎት እውነተኛ ትርጉም አራት ደረጃዎችን ይዟል፦
   ሀ. እግዚአብሔር በፈቃዱ መሠረት የሆነ ነገር ለማድረግ ይወጥናል—6፡10።
   ለ. ፈቃዱን እናውቅ ዘንድ ፈቃዱን በመንፈስ በኩል ይገልጥልናል።
   ሐ. ፈቃዱን ወደ እርሱ በጸሎት መልሰን እናስተጋባለን—ዮሐ. 15፡7።
   መ. እግዚአብሔር ሥራውን የሚያከናውነው በፈቃዱ መሠረት ነው—ራእ. 4፡11።
2. በእግዚአብሔር የተነሳሱ ጸሎቶች እና እርሱ ያነሳሳውን ማስተጋባት ብቻ መንፈሳዊ ዋጋ አላቸው፤ እንደዚህ ዓይነቱን ጸሎት መጸለይን መማር አለብን—ኤፌ. 6፡18፤ 1 ዮሐ. 5፡14-16።

ለ. ያቤጽ ድንበሩን እንዲያሰፋለት እግዚአብሔርን ጠራ፤ በጸሎቱ ውስጥ ያለው የመልካሚቱ ምድር ድንበር መስፋት የመልካሚቱ ምድር እውነታ የሆነውን ክርስቶስን የማትረፍ እና የክርስቶስ ድሰታን ድንበር መስፋትን ያመለክታል—1 ዜና 4፡10፤ ተዛ. ፊልጵ. 3፡8-14።

**VII. ከ 2ኛ ዜና 20፡15-22 ጌታን በማወደስ በመንፈሳዊ ውጊያ መሳተፍን መማር እንችላለን፦**

ሀ. በ 2ኛ ዜና 20፡15 ያሕዌ ለንጉሥ ኢዮሣፍጥ፣ “ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእናንተ አይደለምና ከዚህ ታላቅ ወገን የተነሣ አትፍሩ፥ አትደንግጡም፣” በቁጥር 17 “እናንተ በዚህ ሰልፍ የምትዋጉ አይደላችሁም” አለው፦

1. ከአገልጋዮቹ ብዙዎቹ የእስራኤልን አምላክ ያሕዌን በእጅግ ታላቅ ድምጽ አወደሱት—ቁ. 19።
2. በዝማሬ እና በውዳሴ መጮኽ ሲጀምሩ፣ ያሕዌ ለጠላቶቻቸው ድብቅ ጦርን አመጠባቸው፣ እነርሱም ተመቱ—ቁ. 22።

ለ. ውዳሴ በእግዚአብሔር ልጆች የሚከናወን ከፍተኛው ሥራ ነው—መዝ. 119፡164፤ ዕብ. 13፡15፦

1. የአንድ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕይወት ከፍተኛው መግለጫ ለእግዚአብሔር ያለው ውዳሴ ነው—መዝ. 146፡2፤ ዕብ. 13፡15፤ ራእ. 5፡9-13፤ 19፡1-6፦

   ሀ. የክርስቲያን ሕይወት በውዳሴ ይንሳፈፋል—ሐዋ. 16፡19-34።

   ለ. ማወደስ ጌታን ለመንካት ሁሉንም ነገር ጥሶ ማለፍ ነው—ራእ. 14፡1-3፤ 15፡2-4።

2. መንፈሳዊ ድል በውጊያ ላይ አይመረኮዝም—በውዳሴ ላይ ይመረኮዛል—2 ዜና 20፡20-22።

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት እና በግል ሕይወታችን፣ ለእግዚአብሔር ፍጹም ውዳሴ ልናቀርብ ያስፈልጋል—መዝ. 22፡22፤ ዕብ. 2፡12።

መ. በተለማመድነው እና በተደሰትነው ክርስቶስ በኩል፣ የውዳሴ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያለማቋረጥ ልናቀርብ ያስፈልጋል—13፡15።

ሠ. “አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥ ለዘላለምም ስምህን አከብራለሁ”—መዝ. 86፡12።

*© 2022 Living Stream Ministry*